SPACE SCIENCE AND GEOSPATIAL INSTITUTE

FROM EARTH TO SPACE . . .

# ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲቲዩት

## አንድሮሜዳ-ዳሎል የወጣቶች ሽልማት

## Youth Andromeda-Dallol Award

## [YADA-2017]

### የውድድር አጠቃላይ መግለጫ ሰነድ



ጥር 2017 ዓ/ም

## አዲስ አበባ

## 1.መግቢያ

ኢትዮጵያ የወጣቶች አገር ናት፡፡ ወጣት ዜጎቿ እንደግለሰብ ከዚያም አልፎ እንደቡድን ተሰባስበው በቴክኖሎጂ ዘርፍ ራሳቸውን አሸንፈው አገራቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉት ርብርብ በርካታ ተግዳሮት ቢኖርበትም ፣ ተስፋ ሰጪ ገፅታን መላበሱ ግልጽ ነው፡፡ በቴክኖሎጂ ዘርፍ የሚካሄዱ ፈጠራዎች ለእውቀት መር ኢኮኖሚያዊ እድገት ሁነኛ አንቀሳቃሽ ሞተር መሆናቸው አያጠያይቅም ፡፡አገራዊ እድገትን እና ሁለንተናዊ ልማትን በላቀ ደረጃ ከማረጋገጥ አኳያ ያላቸው ሚናም ቢሆን በጣም ከፍተኛ ነው፡፡በዚህ ረገድ ወጣቶች እንደ አገር ብሎም እንደዜጋ በግልም፣ በጋራም ለሚያደርጉት ልባዊ ጥረት፣ ድጋፍ መስጠት ማድነቅም ፣ ማመስገንም ተገቢ ነው፡፡ ይህ አድናቆት እና ምስጋናም ፣ የተነሳሱትን ወጣቶች ልብ ያሞቃል፤ የሌሎችን ልብ ያነቃቃል፡፡በመሆኑም ማድነቅ እና ማመስገንን ሁሉም ሊያደርገው ቢገባም ፣ እና ጠቀሜታው ግልጽ ቢሆንም ፣በዘርፉ ኋላፊነት የተሰጣቸው መንግስታዊ ተቋማት ሲያከናውኑት ፣ ወጥ ፕሮግራም ቀርጾው ሁለንተናዊ ገፅታ አላብሰው ሲፈፅሙት ደግሞ ፣ የበለጠ ትርጉም፣ የበለጠ ዋጋ ይኖረዋል፡፡

የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት በዚሁ መነሻ በአዋጅ የተሰጠውን ኋላፊነት መሠረት በማድረግ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ የንግድ ሥራ ፈጠራ ሀሳብ አመንጪ ወጣቶች የፈጠራ ሀሳባቸውን ወደምርትና አገልግሎት በማሸጋገር ሂደት የሚገጥማቸውን ፈተና ተቋቁመው ወደተግባር ማሸጋገር እንዲችሉ [Youth Andromeda - Dallol Award YADA 2017] በሚል ርእስ በየዓመቱ የሚካሄድ ልዩ ውድድር አዘጋጅቶ ፣ ወደትግበራ ተሸጋግሯል፡፡

ይህ ሽልማት ወጣት ኢትዮጵያውያን በአገር አቀፍ ደረጃ እንደ ግለሰብ ፣ ለሚያፈልቁት አዲስ ወይም የተሸሻለ የንግድ ሥራ ፈጠራ ኋሳብ እውቅና ከመስጠት ባሻገር ሀሳቦቻቸውን ወደምርትና አገልግሎት መለወጥ እንዲችሉ ተግባራዊ ድጋፍ መስጠትን አካቶ የያዘ ነው፡፡ በመሆኑም በቴክኖሎጂ ዘርፉ እንደአገር ማትጊያና ማበረታቻ ሥርዓት የሚፈጥር ሲሆን ፣ ለሌሎችም ምሳሌ ሊሆን የሚችል በጎ ጥረት፣እና ጅማሮ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡በቴክኖሎጂ መስክ ለሚታዩ ችግሮች በፈጠራ የታገዘ ቴክኖሎጂያዊ መፍትሔ የማስገኘት ውድድር የማዘጋጀቱ ዋነኛ ምክንያትም ከዚሁ የሚነሳ ነው፡፡

## 2. የውድድሩ ጭብጥና ዓላማ

### 2.1.የውድድሩ ጭብጥ

የዚህ ውድድር ዋና ጭብጥ በስፔስ እና ጂኦስፓሻል ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ ውጤታማ የንግድ ሥራ ፈጠራ ሀሳብ አፍላቂ ወጣቶች ሀሳቦቻቸውን ወደ ምርትና

አገልግሎት በማሸጋገር ወደገበያ ማስገባት የሚያስችላቸውን አስፈላጊ ድጋፍ መስጠት ነው፡፡በዚህም ወጣቶች ለራሳቸው የስራ እድልና የገቢ ምንጭ ከመፍጠር ባለፈ የማኅበረሰባቸውን ችግር በመፍታት አዲስ ወይም የተሻሻሉ ምርቶችና አገልግሎቶችን ለገበያ በማብቃት ተወዳዳሪነትን የሚፈጥሩበት ምቹ መደላደል ይጎለብታል፡፡የስራ እድልን በማስገኘት ሳይወሰን በሂደት ኢትዮጵያ በውጭ ምንዛሪ ከውጭ የምታስገባቸውን ምርቶች በመተካት ወይም ወደውጭ አገር በመላክ የውጭ ምንዛሪ ግኝቷን ማሳደግ የሚያስችል የወጣቶች አቅም ግንባታ እርምጃ ነው፡፡

### 2.2.የውድድሩ ዓላማ፣

የዚህ ውድድር ዓላማ በስፔስ እና ጂኦስፓሻል ዘርፍ የሠለጠኑ ወጣቶች ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ የንግድ ሥራ ፈጠራ አመንጪዎች ሃሳቦቻቸውን ወደ ምርትና አገልግሎት በማሸጋገር ወደገበያ መግባት የሚያስችላቸውን ዘርፈ-ብዙ ድጋፍ ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

## 3. የውድድሩ አዘጋጅ፣ የአሰራር ሂደት እና ጊዜ

### 3.1. የውድድሩ አዘጋጅ

ይህ የውድድር ፕሮግራም የተዘጋጀው በ ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሺያል ኢንስቲቲዩት ነው፡፡

- የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲቲዩት ለውድድሩ ተሳታፊና አመልካቾች ውድድሩን በሚመለከት ማንኛውም አስፈላጊ የዶክመንትና መረጃ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- አመልካቾች ለውድድሩ ለሚያቀርቧቸው ማመልከቻዎች ግብዓት የሚሆኑት የቅጽና የሠነድ መረጃዎች በኢንስቲትዩቱ ድረ-ገጽ በኢንተርኔት መረብ ላይ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል ፣
- ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቧቸውን ማመልከቻዎች መቀበልና የውድድሩን ሂደት የሚያሳልጡ እገዛዎችን ያደርጋል፣

- ውድድሩ የሚገዙባቸው መመሪያዎች፣ውሎች በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ እንዲሰራጩ ያደርጋል፡፡

## 3.2. ለውድድሩ የሚቀርቡ የቴክኖሎጂ ዘርፎች

ውድድሩ የሚካሄድባቸው የስፔስ እና ጂኦስፓሻል ቴክኖሎጂ ዘርፎች በዋናነት የሚከተሉትን ያካተተ ሲሆን በእነርሱ ብቻ የተገደበ ግን አይደለም፡፡

1. ሪሞት ሴንሲንግ ቴክኖሎጂ እና አፕሊኬሽን፣
2. ጂኦስፓሻል አናሊቲክስ ፣
3. ናቪጌሽን እና ፖዢሽኒንግ፣
4. ኤሮስፔስ ቴክኖሎጂ ፣
5. ጂኦስፓሻል አርተፊሻል ኢንተሊጀንስ፣
6. ሳተላይት ዳታ አናሊቲክስ፣
7. ቴሌስኮፕ ቴክኖሎጂ፣

## 3.3. የውድድሩ የአፈጻጸም የጊዜ ሰሌዳ፡-

- የውድድሩ ከጥር 19 እስከ የካቲት 19 ቀን 2017 ዓ.ም ባሉት ቀናት የተወዳዳሪዎች ምዝገባ ይካሄዳል፡፡
- የተወዳዳሪነት ምዝገባ ጊዜ ማጠናቀቂያ የመጨረሻ ቀን ተከትሎ ያለት 30 ቀናት ተወዳዳሪዎች የንግድ ሥራ ፈጠራ ኃሳብ ሰነዶቻቸውን በመወዳደሪያ ቅጹ መሠረት የሚያቀርቡበት ጊዜ ይሆናል፡፡
- መወዳደሪያ የንግድ ስራ ፈጠራ መግለጫ ሠነድ ለስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን በ40 ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡
- በውድድሩ ለመሳተፍ የሚፈልጉ አካላት በተቀመጠው የምዝገባ ጊዜ ገደብ መሠረት በኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲቲዩት ዋና መ/ቤት በግንባር በመቅረብ ወይም በኢንስቲትዩቱ ድረ - ገጽ አማካኝነት የቀረበውን የመወዳደሪያ ማመልከቻ ቅፅ በመጠቀም በመሙላት ምዝገባ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
- አመልካቾች ውድድሩን የተመለከቱ ማንኛውንም ሰነድና ተጨማሪ መረጃ ከኢንስቲትዩቱ ዋና መስሪያ ቤት በስልክ፣ በኢሜይል ወይም በግንባር በመቅረብ በመጠየቅ ማግኘት ይችላሉ፡፡

- የምዝገባ ጊዜው ከአለፈ በኋላ የሚቀርቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም፡ ፡

## 3.4. በውድድሩ ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፣

ዋና መስፈርት

ይህ ውድድር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ላላቸው አመልካቾች እና እድሜያቸው ከ 18 እስከ 35 ዓመት ለሚሆናቸው ወጣቶች ሁሉ ክፍት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ዋና መስፈርት እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ ቀጥሎ የተመላከቱ **የማኅበረሰብ ክፍሎች** ለውድድሩ እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ፡፡

- **የዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች**
- **ወጣት ሴቶች ተመራማሪዎችና የፈጠራ ሰዎች**
- **አካል ጉዳተኛ ተመራማሪዎችና የፈጠራ ሰዎች**

## 4.የምዝገባ ሂደት

- በውድድሩ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ተወዳዳሪዎች ከዚህ ሠነድ ጋር ተያይዞ በቀረበው የምዝገባ ቅጽ መሠረት መመዝገብ ይኖርባቸዋል፣ እዝል-1 የምዝገባ ቅጽ፣1"Annex, (registration Form)
- የምዝገባ ቅፁን ሞልተው የተመዘገቡ የውድድሩ ተሳታፊዎች መወዳደሪያ የንግድ ስራ ፈጠራ ፕሮጀክት ሀሳባቸውን እዝል-2 Annex 2( Business Proposal Submission Format)በመጠቀም ያቀርባሉ፡፡
- መወዳደሪያ ሥራዎች የሚቀርቡት በዚህ ሰነድ /Annex 2 ቅጽ/ መሠረት በኮምፒዩተር ተተይቦ ሲሆን የማቅረቢያ ቋንቋ አማርኛ ወይም እንግሊዘኛ መሆን ይችላል፡፡
- የንግድ ሥራ ፈጠራ ሀሳቡ መግለጫ ሠነድ በፁሁፍ የሚቀርበው ለስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲቲዩት ሲሆን በግንባር የሚቀርቡ ማመልከቻዎች በሠም በታሸገ ኤንቨሎፕ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

- አመልካቾች መወዳደሪያ ስራዎቻቸውን ከማቅረባቸው በፊት ቀጥሎ የተመለከቱት ወሳኝ ጉዳዮችን በሥራዎቻቸው ያካተቱ መሆኑን ማረጋገጥ ይገባቸዋል፡፡
  - ✓ የንግድ ሥራ ሃሳቡ ዝርዝር ቴክኒካዊ መግለጫ
  - ✓ የቢዝነስ አዋጪነት ዝርዝር መግለጫ
  - ✓ የግብዓት ፍላጎት ዝርዝር መግለጫ

## 5.የግምገማና መረጣ ሂደት

- በሁሉም ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡት ቴክኖሎጂን መሠረት የንግድ ሥራ ፈጠራ ሀሳብ መግለጫ ሠነድ ላይ በኢንስቲቲዩቱ በሚያዋቅራቸው ገምጋሚ ቡድኖች አማካኝነት በሁለት ምእራፎች የተዋቀረ የግምገማ ተግባር ይከናወናል፡፡

- በመጀመሪያ ደረጃ በሚካሄደው የግምገማ ሂደት ላይ የሚሳተፉት ገምጋሚዎች የሚዋቀሩት ከኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች መካከል ሲሆን የግምገማቸው ዋነኛ ምልከታ የሚደረገው አመልካቾች በጽሁፍ ባቀረቡት በስፔስ እና ጂኦስፓሺያል ቴክኖሎጂ ዘርፍ ወደ ምርትና አገልግሎት ለማሸጋገር ባቀዱት የንግድ ሥራ ፈጠራ ኃሳብ ላይ ይሆናል፡፡

- በመጀመሪያውም ምዕራፍ ግምገማ በአንፃራዊነት ውጤታማነቱ ያመዘነና የተሻለ ሥራ ያቀረቡ 10 የመጀመሪያ ዙር ተወዳዳሪዎች በነጥብ ተለይተው ለቀጣይ ዙር ያልፋሉ፡፡

- በሁለተኛ ደረጃ የሚከናወነውን ሁለተኛ የግምገማ ምዕራፍ የሚያካሂዱት የግምገማ ቡድን አካላት የሚዋቀሩት ከኢንስትቲዩቱ ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን ጭምር በማካተት ይሆናል፡፡

- በሁለተኛው ምእራፍ ግምገማ ከመካሄዱ በፊት በመጀመሪያው ዙር ብልጫ ያገኙት 10 ተወዳዳሪዎች አንድ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረገ የንግድ ሥራ ሀሳብ ስለማመንጨትና ወደ ገበያ ስለማሸጋገር ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ለ10ም ተወዳዳሪዎች ይሰጣል፡፡

- ስልጠናው የውድድሩ ተሳታፊዎች ተስፋ ሰጭና ጠቃሚ የፈጠራ ሥራዎችን ለማፍለቅና ወደገበያ ለማውጣት በሚደረገው ሂደት ውስጥ መከተል ስለሚኖርባቸው አቅጣጫና መውሰድ ስለሚኖርባቸው ቁልፍ ጉዳዮችና እርምጃዎች ግንዛቤያቸውን እንዲያሳድጉ መልካም አጋጣሚ መፈጠርን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

- በሁለተኛው ምእራፍ ግምገማ በመጀመሪያው ዙር ብልጫ ያገኙት 10 ተወዳዳሪዎች ያቀረቡዋቸውን የንግድ ሥራ ሀሳቦች ቴክኒካዊ መፍትሄዎች በተመለከተ የቃል ገለፃ ወይም ያቀረቡትን መግለጫ እንዲያብራሩ ፣ እንዲያስረዱና እንዲተነትኑ ይደረጋል፡፡

- በአዋጪነታቸው፣ በተሻሻለ ቴክኒካዊ መፍትሄዎቻቸው ልቀው የተገኙ ሦስት /3/ ውጤታማ አመልካቾች የዓመቱ አሸናፊ ሆነው ለድጋፍ ይመረጣሉ፡፡

### ሀ. በሚቀርቡ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ስለሚካሄድ የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ፣

- ለውድድሩ የሚቀርቡ ሁሉም የመወዳደሪያ ሥራዎች በስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሺያል ኢንስቲቲዩት ግምገማ ይደረግባቸዋል፡፡ በዚህ በመነሻ ከቀረቡ አጠቃላይ ስራዎች መካከል በቁጥር እስከ 10 የሚደርሱ የተወዳዳሪዎች ሥራዎች ይለያሉ፡፡

- ስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሺያል ኢንስቲቲዩት በሰነዶቹ ላይ ያካሄደውን ግምገማ በተመለከተ በውጤት የተደገፈ ሪፖርት በማዘጋጀት ውጤቱን የቃል ገለፃ ከሚደረግበት ጊዜ አስቀድሞ ኢንስቲትዩቱ የበላይ አመራር ያቀርባል፡፡

- የግምገማ ቡድን አባላት በተወዳዳሪዎች የሚቀርቡ ሥራዎችን በሚከተሉት መስፈርቶችና የክብደት አመልካቾች ይገመግማሉ፡፡

    - በስፔስና ጂኦስፓሺያል ቴክኖሎጂ ዘርፍ ውስጥ የሚታይ ችግርን ለመለየት የተደረገ ትንተና 20%

    - ችግሩን ለመፍታት በቀረበው ቴክኒካዊ መፍትሄው ውስጥ የተካተተ የመሻሻል ደረጃ፣ /Degree of Innovation/ 20%

- የተግባራዊነት ብቃት /Practical applicability 30%
- የንግድ አዋጪነት እና ዘላቂነት ደረጃ 20%
- ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አኳያ የንግድ ፈጠራ ሀሳቡ ያለው ትስስር 10%

## ለ. በተለዩ 10 የተወዳዳሪዎች ሥራ ላይ የሚደረግ ግምገማ

የተለዩ 10 ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቧቸውን ሥራዎች ለማጥራት ወይም ማሻሻያዎችን ለማድረግ እንዲችሉ ስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት አማካኝነት ተጋብዘው የህግና የቴክኒክ ምክር አገልግሎት እንዲሁም የተለያዩ የመረጃ ምንጮች የአእምሯዊ ንብረት መረጃን ጨምሮ ለመረዳት የሚያግዙ ምልከታዎችን /Search tools/ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- ተወዳዳሪዎች የመጨረሻ ደረጃ ሥራዎቻቸውን /final entry/ ቀደም ሲል በተገለፀው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተወዳዳሪዎች የመጨረሻ ደረጃ በፈጠራ የታገዘ ቴክኒካዊ መፍትሄ ሰነዶቻቸውን አጠናቅቀው ማቅረብ እንዲችሉ ኢንስቲዩቱ የግብዓት፣ እና የቴክኒክ ምክር እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
- በተለዩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ በፈጠራ የታገዘ ቴክኒካዊ መፍትሄ ፕሮጀክቶች ላይ ከ 15 - 20 ደቂቃ ለሚሸፍን ጊዜ ተወዳዳሪዎች የቃል ገለፃ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ገለፃው ከተካሄደ በኋላ የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜ ይኖራል ፡፡የገለፃ፣ የጥያቄና መልስ ሂደቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ከ10 ተወዳዳሪዎች መካከል የተሻለ ሥራ ያቀረቡ 3 ተወዳዳሪዎች ዝርዝር ይፋ ይደረጋል፡፡
- በዚህ ምዕራፍ የሚካሄደውን ግምገማ የሚመራው በኢንስቲትዩቱ እና ከኢንስቲትዩቱ ውጭ ያሉ ባለሙያዎችን በተካተቱበት ገምጋሚ ቡድን ሲሆን በቁጥርም እስከ 7 አባላት ድረስ ሊያካትት ይችላል፡፡

በሁለተኛው የግምገማ ምዕራፍና የመጨረሻ ሂደት የሚመረጡ ቴክኒካዊ መፍትሄዎች ቀጥሎ ባሉት የክብደት መጠን ዳግም እንዲመዘኑ ይደረጋል፡፡

- **ወጥነት (Orginality) 20%**
- **የንግድ ሥራ ሀሳቡ ወደ ተግባር የመሸጋገር እድሉ ከቴክኒካዊ ይዘቱ እና ከኢኒስቲትዩቱ ተጨባጭ አቅም አኳያ ሲፈተሽ 30%**
- **የኢንተርፕሩነርሺፕ ክህሎት 25%**
- **የንግድ ስራ ፈጠራ ሃሳቡ የትርፋማነት እና የሥራ እድል የመፍጠር አቅሙ(Potential) 25%**

## 5.ለውድድሩ ተሳታፊዎች የሚሰጡ የማበረታቻ ሽልማቶች /Awards/

በግምገማው ሂደት የተለዩ ሁሉም ከ1ኛ እስከ 3ኛ ደረጃ ለተቀዳጁ ተወዳዳሪዎች ቀጥሎ የተመለከቱትን ሽልማቶች ያገኛሉ፣

- ❖ የውድድሩ አሸናፊ ለመሆናቸው የማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ሜዳሊያ ፣
- ❖ የቀረቡ ሥራዎች በግምገማ ቡድኑ የአእምሯዊ ንብረት መብት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆናቸው ከተገለፀ በብሔራዊ ደረጃ ለሚደረግ ምዝገባ ማመልከቻና ምርመራ /filing and examination fees/ ክፍያ ይፈፀምላቸዋል፣
- ❖ አሸናፊዎቹ በተወዳደሩበት ሠነድ በተገለፀው ዝርዝር መሰረት የቁሳዊ ግብአት አቅርቦት በግዢ ይፈፀምላቸዋል
- ❖ በየሶስት ወራት ከውጤት መግለጫ ጋር ተገናዝቦ በሚደረግ ግምገማ የሚወሰን ሆኖ እስከሁለት ዓመት የሚዘልቅ ያለክፍያ የስራ ቦታ ይመቻችላቸዋል
- ❖ የመብራት ፣ የኢንተርኔት ፣የጠረጴዛ ወንበርና ተዛማጅ መገልገያዎች (Utilities) ይመቻችላቸዋል
- ❖ የቴክኖሎጂ ምክር አገልግሎት
- ❖ ፕሮጀክት ማኔጅመንት እና የቢዝነስ ደቨሎፕመንት ስልጠና
- ❖ የስነ-ልቦና ግንባታ እና የማነቃቂያ ስልጠናዎች
- ❖ የማርኬቲንግ እና ብራንዲንግ ሥልጠና

- ❖ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር መገናኘት የሚያስችላቸው የትስስር መድረክ እንዲሁም የኢግዚቢሽን ተሳትፎ ማመቻቸት
- ❖ ውሱን የትራንስፖርት መሸፈኛ አበል እና የመስክ ስራ አበል አቅርቦት ያገኛሉ፡ ፡

## 6.ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጐች

6.1. የውድድሩ ባለቤትነት እና ምሥጢር ጠባቂነት

የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻያል ኢንስቲቲዩት ውድድሩን በተመለከተ

ሀ. የባለቤትነት መብት አለው፣

የስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ውድድሩን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የማቋረጥና የመሰረዝ መብት አለው፡፡

**ለ. ሚስጥር መጠበቅና ለሌላ 3ኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት ስምምነት**

- ➢ ይህን ውድድር ያዘጋጀው የስፔስ ሳይንስና የጂኦስፓሺያል ኢንስቲቲዩት ሲሆን፡ የውድድሩ አዘጋጅ አካላት ወይም ገምጋሚ አባላት ሚስጢር የመጠበቅና ለ3ኛ ወገን አሳልፎ ያለመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡
- ➢ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ የንግድ ሥራ ፈጠራ ሀሳቦቹን በተመለከተ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ የሀገሪቱ ህግ በሚደነግገው መሠረት ፈጠራውን የማስጠበቅ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡

**ሐ.. የመብት ጥሰትን በተመለከተ፣**

- ➢ የመብት ጥሰትን የመከላከል ሙሉ ኋላፊነት የተወዳዳሪውና የተወዳዳሪው ብቻ ነው፡፡

## 6.2. ለውድድር በቀረቡ ማመልከቻዎች የተካተቱ  መረጃዎችን በተመለከተ፣

- ➢ የውድድሩ ተሳታፊዎች ለውድድር ባቀረቡዋቸው ሰነዶች ውስጥ የተካተቱ ፈጠራዎቻቸውን ቅጅ በእጃቸው ማስቀረት ይኖርባቸዋል፡፡

- ለውድድር የቀረቡ የወረቀትም ሆነ የኤሌክትሮኒክ መረጃዎች ለተወዳዳሪዎች ተመላሽ አይሆኑም ፡፡

- ሁሉም የቀረቡ የውድድር መረጃዎች ከውድድሩ መጠናቀቅ በኋላ በጥብቅ ሚስጥር እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

## 6.3. የህጎቹ የተቀባይነት ወሰን ፣

- ማንኛውም የውድድሩ ተሳታፊ ለዚህ ውድድር አፈፃፀም የቀረቡ መመሪያዎችን ለውድድር ሲመዘገብ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡

## 6.4. አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት አግባብ

- በዚህ የውድድር ሂደት የሚነሱ ክሶች፣ አለመግባባቶች ወይም ቅሬታዎች ባሉበት ሁኔታ የሚፈቱ ካልሆነ የሚታዩት ለዚህ ሲባል ኢንስቲትዩቱ በሚያዘጋጀው የቅሬታ ሰሚ ኰሚቴ ይሆናል።

## 6.5. ከውድድር አሸናፊዎች ጋር ስለሚፈጸም ውል

- የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስትቲዩት ከውድድሩ አሸናፊዎች ጋር በተናጠል መብት፣ ግዴታ እና ኃላፊነትን በተመለከተ ውል ይፈጽማል፤
- በተዋዋይ ወገኖች የሚፈጸመው የውል ሰነድ ይዘት አሸናፊዎች ከተለዩ በኋላ የሚገለጽ ሆኖ፤ በተዋዋዮች ፊርማ የሚጸና ይሆናል፡፡